# ቅኔ ከድሮ

## ዋለልኝ መኮንን (1968)*

መይሳው ካሳ መካር አጡ;
እንዳይሆን ሆነው ቀበጡ;
ብዙ እያወቁ እንደጅል;
የማይሆን ነገር መከጀል;
ለድሃ እንዳይሆን እያወቁ;
ዘውድ እምጡ ብለው ደረቁ::
---------
ከለበሱ አይቀር ሱሪ;
የጥንቱን ነበር የተፈሪ;
ግና አይመችም ለስራ;
አጣብቆ ይዞ በቀኝ በግራ::

## ደንዳር ደንሳሞ (1968)

ባውዳመቱ ዋዜማ;
ስሰማ ከርሜ ላህየ ዜማ;
በመጨረሻ ሲደክመኝ;
ጉዋደኞቼ መከሩኝ;
ሊነጋ ነው እሉኝ;
አሮጌ ዘመን ልንሸኝ::

## ጸገየ ወይን ገብረመድህን (1968)

ነፎ መስዬ እባያ;
ባዶ እጀን ቆሜ ከገበያ;
አንገበገበኝ ንደቱ;
ሲሸጥ ሲለወጥ ማየቱ;
ብዙው በርካታው በጥቂቱ::

---

* እ. ኤ. አ.